# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት

## ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ

## DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

## SOUTH ETHIOPIA REGION STATE

፪ኛ ዓመት ቁጥር 7
አርባምንጭ ታህሳስ 5 ቀን

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No 7
Arbaminch December,


**አዋጅ ቁጥር ፲፪ / ፳፻፲፮ ዓ.ም**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮን ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ**

**መግቢያ**

ሕገ መንግስቱን እና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን እንዲሁም የሕግ የበላይነትን የሚያስከብር፤ ወጥነት ያለው ውጤታማና ቀልጣፋ አገልግሎት የሚሰጥ፤ የሕዝብንና የመንግስትን ጥቅም በተሟላ ሁኔታ የሚያስጠብቅ አንድ ጠንካራ ሕግ አስከባሪ የዓቃቤ ሕግ ተቋም ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ

**PROCLAMATION No 12/2023**

**A Proclamation to Organize and Determine Powers and Functions of the South Ethiopia Regional State Justice Bureau**

**Preamble**

**WHEREAS,** it has been found necessary to establish one strong law enforcement public prosecution institution which can comprehensively protect public and government interest and deliver unvarying, effective and efficient service as well as enforcing the constitution and constitutional systems and the supremacy of law;

በመገኘቱ፤

የሕዝብ ተዓማኒነት ያለው፣ በተሟላ ተቋማዊና ሙያዊ ነፃነት የሚያገለግል እንዲሁም ለሙያዊ፣ ተቋማዊና ሕዝባዊ ተጠያቂነት የሚገዛ፣ በግልጽነትና በአሳታፊነት የሚሰራ የዓቃቤ ሕግ ተቋም በማስፈለጉ፤

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀፅ ፶፬ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### አንቀጽ ፩ አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ **"የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የፍትህ ቢሮን ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፪ / ፳፻፲፮"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ ፪ ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር፤

፩) **"ክልል"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ነው፤

፪) **"ምክር ቤት"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት ነው፡፡

፫) **"መስተዳድር ምክር ቤት"** ማለት በደቡብ

**WHEREAS**, it has been found necessary to organize public prosecutor institution with full institutional and professional independency as well as to govern the professional, institutional, and public accountability;

**Now, therefore**, in accordance with Article 54/3-a/ of the Constitution of the Region, the State Council hereby Proclaimed as follow.

## PART ONE

## GENERAL

### Article 1 Short Title

This Proclamation may be cited as **'The Organaization and Determination Of Power and Functions of the South Ethiopia Regional State Justice Bureau Proclamation No 12/2016'**

### Article 2 Definition

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1) **"Region"** means the South Ethiopia Region;
2) **"Council"** means the South Ethiopia State Council;
3) **"Executive Council"** means the highest Executive Organ of the region

ኢትዮጵያ ክልል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 67 መሠረት የተገለጸው የክልሉ ከፍተኛ የአስፈፃሚ አካል ነው፡፡

፬) **"አስተዳደር ምክር ቤት"** ማለት እንደአግባብነቱ በየደረጃው በሚገኙ የአስተዳደር እርከን የአስፈፃሚነት ተግበራን የሚመራ የካቢኔ አባላትን የያዘ አስፈፃሚ አካል ነው፡፡

፭) **"የመንግስት መስሪያ ቤቶች"** ማለት ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በክልሉ መንግስት በጀት የሚተዳደሩ አካላት ሆነው የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅቶችንም ይጨምራል፡፡

፮) **"ሕግ"** ማለት በፌደራል መንግስት ሕግ አውጪ አካል ወጥተው በክልሉ ውስጥ ተፈጻሚነት ያላቸው የሕግ ማዕቀፎችን፣ በክልሉ ሕግ አውጪ አካላት የወጡ አዋጆችን፣ ደንቦችን እና ስልጣን በተሰጣቸው የክልሉ መንግስት አካላት የወጡ መመሪያዎችን ያጠቃልላል፡፡

፯) **"ሕገ-መንግስት"** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ሕገ-መንግስት ማለት ነው፡፡

፰) **"የወንጀል ሕግ"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ህዝብ

as provided under Article 67 of the Constitution of the the South Ethiopia Regional State;

4) **"Administrative Council"** means an executive body consisting of cabinet members that directs the executive functions of the Regional State at various levels, as appropriate;

5) **"Government Offices"** means organs with legal personality administered wholly or partly by the State budget, including the developmental organizations of the State;

6) **"Law"** means legal frames that are issued by the Federal Government Legislative Organ applicable in the Region, Proclamations and Regulations issued by the Regional Legislative organ and includes Directives issued by the authorized organs of the Regional State;

7) **"Constitutions"** means the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the South Ethiopia Regional State Constitution;

8) **"Criminal Law"** means the criminal

ተወካዮች ምክር ቤት የተደነገገ የወንጀል ሕግ ነው፡፡

፱) **“ቢሮ ”** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ ነው፤

፲) **“ቢሮ ኃላፊ”** ማለት የፍትህ ቢሮ ኃላፊ ነው፤

፲፩) **“ምክትል ቢሮ ኃላፊ”** ማለት የክልሉ ፍትሕ ቢሮ ምክትል ኃላፊ ነው፤

፲፪) **“ዐቃቤ ሕግ”** ማለት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሰረት የሚቀጠር ወይም የሚመደብ እና የሚተዳደር የሕግ ባለሙያ ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ መሠረት የተሾሙ የፍትሕ ቢሮ ኃላፊን፣ ምክትል ቢሮ ኃላፊንና እና በየእርከኑ ያሉ የፍትህ መምሪያ ወይም ጽህፈት ቤት ኃላፊዎችንም ይጨምራል፤

፲፫) **“ፖሊስ”** ማለት የፌደራል ወይም የክልል ፖሊስ ነው፡፡

፲፬) “**ሰው**” ማለት በተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፭) በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፡፡

law provided by the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

9) “**Bureau**” means South Ethiopia Region State Justice Bureau;

10) **“Head of the Bureau”** means head of the Justice Bureau;

11) **“Deputy Head of the Bureau”** means deputy head of the Justice Bureau;

12) “**Public Prosecutor”** means a lawyer employed or assigned and administered under Regulation to be issued by the Executive Council and includes head of Jusctice Bureau, the deputy head of Justice Bureau and includes head at each level like Justice Department or Office appointed in accordance with Article 7 of this Proclamation;

13) “**Police”** means Federal or Regional Police;

14) “**Person**” means a natural or a legal person;

15) Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## ክፍል ሁለት

## አደረጃጀት፣ ተጠሪነት፣ ሥልጣን እና ተግባር

**አንቀጽ ፫ አደረጃጀት**

“የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ ከዚህ በኋላ “ፍትህ ቢሮ” እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተደራጅቷል፡፡

**አንቀጽ ፬ ዋና መስሪያ ቤት**

የፍትህ ቢሮ ዋና መስሪያ ቤት ሳውላ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ የምድብ ጽህፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፭ ተጠሪነት**

፩) ቢሮው ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ እና ለመስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል፤

፪) የዞን የፍትህ መምሪያ ተጠሪነቱ ለፍትህ ቢሮ፣ ለዞኑ አስተዳዳር እና አስተዳደር ምክር ቤት ይሆናል፤

፫) በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር ያሉ የፍትህ ጽህፈት ቤቶች ተጠሪነታቸው ለዞን ፍትህ መምሪያ እና በየአስተዳደር እርከን ለሚገኝ ዋና አስተዳደሪ እና አስተዳደር ምክር ቤት ይሆናል፤

፬) የክልሉ ፍትህ ቢሮ ኃላፊ በክልሉ በየትኛውም ደረጃ ለሚገኝ ዐቃቤ ሕግ

## PART TWO

## Organization, Accountability, Powers and Functions

**Article 3 Establishment**

"The Justice Bureau of the South Ethiopia Regional State, hereinafter referred to as the "Justice Bureau", is hereby organized as a government office with independent legal personality.

**Article 4 Head Office**

Head Office of Justice Bureau shall be in Sawula City and may have branch offices in other cities of the region, as may be necessary.

**Article 5 Acountability**

1) The Bureau shall be accountable to the Chief Executive and Executive Council;
2) Justice department shall be accountable to the Justice Bureau and to the Zonal Chief Adminstrator and Admnistrative Council;
3) Justice office in woreda or city administration shall be accountable to Zonal Justice Department, chief City Administrator and Administrative Council;
4) The head of the Justice Bureau is the head of the public prosecutor at any level in the

የበላይ ኃላፊ ነው፤

፭) በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፬ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በየትኛውም ደረጃ ያሉ ዐቃቤያነ ሕግ ለበላይ ኃላፊያቸውና ለተመደቡበት የስራ ዘርፍ ኃላፊዎቻቸው ተጠሪ ይሆናሉ፡፡

Region;

5) Without prejudice to Sub Article 4 of this Article, Public prosecutor at all level shall be accountable to their principal head and to the division heads they are assigned;

**አንቀጽ ፮ ሥልጣንና ተግባራት**

የፍትህ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) በሕግ ጉዳዮች የክልል መንግስት ዋና አማካሪ እና ተወካይ ሆኖ ይሰራል፤

፪) በፌደራል መንግስት ተዘጋጅቶ የጸደቀውን የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

፫) የወንጀል ፍትሕ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተንና ማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ያስፈፅማል፤

፬) በፌዴራልና በክልሉ ሕገ-መንግስታት እና በሌሎች ሕጎች የተደነገጉ የግልና የቡድን መሰረታዊ መብቶች እና ነፃነቶች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

**Article 6 Powers and Functios**

The Justice Bureau shall have the following powers and Functions:

1) Works as principal advisor and representative of the Regional State regarding law;
2) Coordinates, follow ups and ensures the implementation of the criminal justice policy in the Region, which is prepared and approved by the Federal Government;
3) Develop and effect to be executed the system that enables to collect, organize, analyze, and disseminate the informations of criminal justice;
4) Ensures the fundamental rights and liberties of the individuals and groups enshrined under Federal and Regional Conistitutions and other laws are respected;

፭) የወንጀል ጉዳይን በተመለከተ፤

ሀ/ በክልሉ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር በሚወድቁ በማናቸውም የፀረ-ሙስና እና የታክስ ህጎችን በመጣስ በሚፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮች እንዲሁም ከባድና ውስብስብ በሆኑ ሌሎች በክልሉ ፖሊስ ምርመራ ዘርፍ የሚከናወኑ የወንጀል ምርመራዎችን ከፖሊስ ጋር አብሮ ያጣራል፤ ምርመራውን በበላይነት ይመራል፤ ይከታተላል፤ ያስተባብራል፤ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤

ለ/ በሕዝብ ጥቅም መነሻ ወይም በወንጀል የማያስጠይቅ ሁኔታ መኖሩ በግልፅ ሲታወቅ የወንጀል ምርመራ እንዲቋረጥ ወይም የተቋረጠው የወንጀል ምርመራ እንዲቀጥል ያደርጋል፤ ማናቸውም የወንጀል ምርመራዎች በሕግ መሰረት መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤ አስፈላጊውን ህጋዊ ትዕዛዝ ለሚመለከተው አካል ይሰጣል፤

ሐ/ ምርመራቸው በፖሊስ በተጀመረባቸው መካከለኛ፣ ቀላል እና በግል አቤቱታ በሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች ምርመራ በአግባቡ ስለመከናወናቸው በቅርበት ክትትል ያደርጋል፤ በተጀመረ የወንጀል ምርመራ አስመልክቶ ፖሊስ ለዓቃቤ ሕግ ማሳወቁን ያረጋግጣል፤

5) Regarding criminal matters:

a) Together with the police office, investigates any criminal cases of violation of anti-corruption and tax laws that fall under the jurisdiction of the Regional Court, as well as other serious and complex criminal investigations carried out in the division of police investigation of the Region; supervise the investigation; follow ups, coordinates and effects a report to be submitted to it;

b) Orders discontinuation or restart discontinued investigation on the basis of public interest or when it is clearly known that there could be no criminal liability, ensures investigation is conducted in accordance with the law, gives the necessary legal order to relevant body;

c) It closely monitors the proper conduct by the police of investigations in moderate, minor, and crimes punishable up on compliant, ensures that the police inform the prosecutor about the criminal investigation that has been initiated;

መ/ በወንጀል መዝገብ ላይ የተሰጠ የዓቃቤ ሕግና የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ለሚመለከተው ፖሊስ ያሳውቃል፤ የወንጀል ምርመራ መዝገቦችን አስመልክቶ በየደረጃው ባሉ ዓቃቤያነ ሕግ በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ በፖሊስ የሚቀርቡ አቤቱታ ተቀብሎ ውሳኔ ይሰጣል፤

ሠ/ የተጠናቀቁ የምርመራ መዝገቦችን ከሕግና ከማስረጃ አንፃር መርምሮ በሥነ-ሥርዓት ሕግ መሰረት የተቀመጡ መመዘኛዎች ሲሟሉ የ'አያስከስስም' ወይም የ'ተዘግቷል' ውሳኔ ይሰጣል፤

ረ/ የጥፋተኝነት ድርድር ይወስናል፤ ድርድር ያደርጋል፤ አማራጭ የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ ይወስናል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ሰ/ መንግስትን በመወከል የወንጀል ጉዳዩች ክስ ይመሰረታል፤ ይከራከራል፤ ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ክስ ያነሳል፤ የተነሳ ክስ እንዲቀጥል ያደርጋል፤

ሸ/ የእጅ ከፍንጅ ወንጀሎች ተፈፅመው ሲገኙ በተፋጠነ ሥነ-ሥርዓት ውሣኔ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

d) Notifies to the relevant police about decisions given on criminal case files by the public prosecutor and court; receives and gives decision on appeals presented by the police against decisions given at different level of the public prosecutions;

e) Reviews completed investigation files based on evidence and law, and gives 'no cause of action' or closing decision where condition provided under the criminal procedure laws are met;

f) determines guilty plea, plea bargaining, decides alternative remedies to be taken; follows its implementations;

g) Institutes criminal case charges by representing the government, litigates, withdraws charge when found necessary in the interest of the public, resumes withdrew charge;

h) Facilitates the speedy trial in crimes cases of flagrante delicto, and collaborates with the police and other

ለዚህም ከፖሊስና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር ተባብሮ ይሠራል፤

ረ/ ለወንጀል ጉዳይ ምስክሮች በወቅቱ መጥሪያ እንዲያደርስና ምስክሮችንም ወደ ፍርድ ቤት እንዲያቀርብ ለፖሊስ ትእዛዝ ይሰጣል፤

ቀ/ የወንጀል ድርጊት ጠቋሚዎችና ምስክሮች በሕግ መሰረት ተገቢውን ጥበቃና ከለላ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

በ/ በማረፊያ ቤትና በማረሚያ ቤት ቁጥጥር ሥር ያሉ ተጠሪጣሪዎችንና ታራሚዎችን ይጎበኛል፤ አያያዛቸው እና ቆይታቸው በሕግ መሰረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፤ ሕገ- ወጥ ተግባር ተፈፅሞ እንደሆነ እንዲታረም ያደርጋል፤ ሕግን ተላልፈዋል በተባሉ ሰዎች ላይ በሕግ መሰረት እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

ተ/ በዕርቅ ሊያልቁ የሚችሉ የወንጀል ድርጊቶች በእርቅ የሚጠናቀቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ቸ/ ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችና ትዕዛዞች መፈፀማቸውንና መከበራቸውን

relevant bodies for this matter;

i) Orders the police to issue summons to witnesses in a criminal case in a timely manner and to bring witnesses to court;

j) Ensure that whistleblowers and witnesses of criminal activity get proper protection and defence in accordance with the law;

k) visits suspected and inmates under custody at police stations and prisons; ensure their handling and stay is carried out in accordance with the law; causes unlawful act to be rectified; take measures or cause measures to be taken based on the law against people who are found to have transgressed the law;

l) facilitates to end criminal acts that can be ended in reconciliation;

m) follows up the implementation and enforcement of judgments and orders given by courts under criminal case; applies to the court that gave judgments

ይከታተላል፤ ሳይፈፀሙ ከቀሩ ወይም አፈፃፀማማቸው ሕግን ያልተከተለ ከሆነ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለሰጠው ፍርድ ቤት በማመልከት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

ኀ/ በፍርድ ቤት የሚወሰኑ የወንጀል ቅጣቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን ያደራጃል፤ ወይም መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፤

ነ/ የሞት ቅጣት ውሳኔዎችን ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት በፌዴራል ፍትህ ሚኒስቴር በኩል እንዲቀርብ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

ኘ/ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያን ላይ የሚፈፀሙ ወንጀል ድርጊቶችን በልዩ ሁኔታ የሚከታተል ልዩ የስራ ክፍል በተቋሙ ያደራጃል፤

፮ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን በተመለከተ፤

ሀ) በክልል የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሕዝብ እና የክልል መንግስት መብትና ጥቅም ወኪል ሆኖ ይከራከራል፤ ያስከብራል፤ እንዲከበሩ ያደርጋል፤

and orders and effects corrective action to be taken where they have not been implemented or their implementation is contrary to law;

n) organizes or ensures the establishment of systems for the proper execution of criminal punishments enforced by the court of law;

o) Causes death penalty decisions to be submitted to the President of the Federal Democratic Republic of Ethiopia through the Ministry of Justice; follows up its execution;

p) organize a special working unit that follow ups criminal activities against members of society that need special attention, especially women, children, persons with disabilities and the elders;

6) Regarding civil matters:

a) litigates, enforces, causes enforcement, follows and supervises the process of enforcement within the Regional Public Offices by acting as an agent of rights

የሚከበሩበትን ሂደት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ለ) ትላልቅ የመንግስት ፕሮጀክቶችን የውል ዝግጅት እና ድርድር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያደርጋል፤ የሕዝብና የክልል መንግስት መስሪያ ቤቶች ጥቅም ይጎዳል ብሎ ሲያምን በሌሎች ጉዳዮች ውል እና የመግባቢያ ሰነዶች ዝግጅትና ድርድር ያደርጋል ወይም የሚመለከታቸውን አካላት ያማክራል፤

ሐ/ የክልል መንግስት መስሪያ ቤቶችን በመወከል የፍትሐብሔር ክስ ይመሰርታል፤ በከሰሰበት ወይም በተከሰሰበት የፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ክርክር ያደርጋል፤ በተጀመረ ክርክር ተቋማትን ተክቶ በተናጠል ወይም በጋራ ይከራከራል፤ ወይም በክርክር አመራር ላይ ለመሥሪያ ቤቶች አቅጣጫ ይሰጣል፤ በሕግ መሠረት ውሳኔዎችን ያስፈፅማል፤

መ/ በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች እና በግል ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች መካከል የሚከሰቱ የፍትሐብሔር ክርክሮች በድርድር እንዲያልቁ ጥረት ያደርጋል፤ ድርድሩ ካልተሳካ ጉዳዩን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቅርቦ

and interest of the People and the Government;

b) advises and participates with concerned bodies in contract preparation and negotiation of mega projects; participates or advises concerned bodies in other contract preparation and negotiation when it believes that public and government interest could be affected;

c) Institutes civil suits on behalf of Regional government offices; argues civil cases in which it sued or she has been sued; argues separately or jointly on behalf of institutions in a debate that has started; or provide direction to offices on dispute management; executes decisions made in accordance with law;

d) It shall endeavor to resolve civil disputes between regional government agencies and private organizations or individuals through negotiation; if negotiation fails, it shall submit the matter to the competent court for litigation;

ይከራከራል፤

ሠ/ የክልል መንግስት መስሪያ ቤቶች እርስ በርሳቸው ያልተግባቡባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ተቋማትን ያደራድራል፤ የህዝብና የመንግስት ጥቅም ሊያረጋግጥ የሚችል ውሳኔ ይሰጣል፤ በውሳኔው መሰረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፤

ረ/ የተመዘበረ የመንግስት ገንዘብ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ ያስመልሳል፤ የሙስና ወንጀል ውጤት የሆኑት እና በፍርድ ሂደት ላይ ያሉ ንብረቶችን ያስተዳድራል፤ እንዲወረስ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ንብረቶች ለሚመለከተው የመንግስት አካል ያስተላልፋል፤

ሰ/ የፍትሐብሔር ክስ ለመመሥረት የገንዘብ አቅም የሌላቸውን ዜጎች በተለይም ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን ወክሎ ይከራከራል፤

ሸ/ የገንዘብ አቅም የሌላቸው የወንጀል ተጎጂ የሆኑ ተበዳዮች እንዲካሱ መልሰው እንዲቋቋሙ እንዲሁም ከጉዳቱ የተያያዙ የፍትሐብሔር ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ እነሱን በመወከል የፍትሐብሔር ክስ ያቀርባል ወይም ይደራደራል።

e) Negotiates the Regional Public Offices in civil suits where they fail to communicate with each other; passes final decision that ensures the people and government interest; ensures as if it is implemented based on the decision passed;

f) Causes the embezzled government assets to be returned by filing a lawsuit in a court of competent jurisdiction; manages assets that are the result of corruption and are on trial; transfers the confiscated assets to the relevant government body;

g) conducts litigation by representing citizens with no means to institute civil suit: specially women, children, disabled and the elderly;

h) File or negotiate civil lawsuits on behalf of indigent crime victims to obtain compensation, rehabilitation, and to protect their civil rights related to the harm;

፯ የሕግ ጥናት፣ ማርቀቅ እና ማስረፅ ሥራን በተመለከተ፤

ሀ/ ከክልሉ መንግሥት ተቋማት የሚመነጩ የሕግ ሀሳቦችን ተቀብሎ ረቂቅ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤ በሌሎች አካላት ተዘጋጅተው ሲቀርቡለት ጥራታቸውን ጠብቆ ያበለጽጋል፤ የተዘጋጁ መመሪያዎችን በተመለከተም ለአሠራር ያመች ዘንድ ተገቢውን ቁጥር ይሰጣል፤ ለህዝብ ይፋ መሆናቸውንም ይከታተላል፤

ለ/ በክልሉ ውስጥ የተለያዩ አካላት የሚያዘጋጇቸው የሕግ ረቂቆች ከሕገ-መንግሥቱም ሆነ ከክልሉና ከፌደራል መንግሥቱ ሕግጋት ጋር የተጣጣሙ ስለመሆናቸው ይከታተላል፤ ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ሙያዊ አስተያየት ያቀርባል፤

ሐ/ የክልሉ መንግሥት ሕጎች ተግባራዊ መደረጋቸውንና አተገባበራቸውም ወጥነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤ የክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች ሥራቸውን በሕግ መሠረት ማከናወናቸውን በቅርብ ይከታተላል፤

መ/ በሥራ ላይ ያሉትን የክልሉ ሕጎች በየጊዜው እያጠና ወይም በሌሎች እያስጠና የሚሻሻሉበትን የውሳኔ ሃሳብ በማዘጋጀት ለክልሉ መንግሥት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም

7) Regarding Legal Study, Drafting and Dissemination

a) Accepts and prepares legal proposals arising from the institutions of the Regional Government and draft proclamation, regulations and directives, and enhances their quality when prepared and submitted to it by other bodies;

b) follows whether the drafts of legislations prepared by other bodies in the region are consistent with both the Constitution and the laws of the region and federal government; provides professional comments on the issues addressed directly to the relevant departments;

c) Ensure that the laws of the Region are implemented and their implementation is consistent; ensures closely that executive bodies of the Region implements its task in consistent with the law;

d) Submit to the Region Government a recommendation for periodic amendments to the laws of the Region in force; when approved, prepare drafts

ለማሻሻያዎቹ የሚያስፈልጉትን ረቂቆችን በማዘጋጀት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሥልጣን አካላት አቅርቦ ያስጸድቃል፤

ሠ/ የሕግ ጉዳዮችን በተመለከተ የክልሉን መንግሥት ተቋማትን ያማክራል፤

ረ/ ዓቃብያነ-ሕግ ስለሥራቸው ያላቸውን አመለካከት፣ እውቀትና ክህሎት በተከታታይና በየደረጃው ለማሳደግ ይቻላቸው ዘንድ ተገቢውን የአቅም ግንባታ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

ሰ/ የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ለክልሉ መንግሥት ባለሥልጣናት፣ ሌሎች ተሿሚዎች፣ የህዝብ ተመራጮች፣ ሠራተኞች፣ እንዲሁም የግሉ ዘርፍ ተሳታፊዎች እንዳስፈላጊነቱ የንቃተ-ሕግ መርሀ-ግብሮችን ያዘጋጃል፤ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

ሸ/ የክልሉንና በክልሉ ውስጥ ተፈጻሚነት ያላቸውን የፌደራል መንግሥት ሕጐችን የማሰባሰብ፣ የማጠቃለልና የኮዲፊኬሽን ሥራ ይሰራል፤ የክልሉን ህጎች በባለአደራነት ይይዛል፣ ያሰራጫል፤

ቀ/ የህብረተሰቡን ንቃተ ሕግ ለማዳበር ለክልሉ ህብረተሰብ በተለያዩ ዘዴዎች የንቃተ ሕግ ትምህርት ይሰጣል፤

of the legislation required for the amendments and submit them to the relevant authorities for approval;

e) Advises the public institutions of the Regional government on legal matters;

f) Makes public Prosecutors receive appropriate capacity building so that they can improve their attitude, knowledge and skills about their work continuously and at every level;

g) Develops and provides or effects trainings to be provided as may be necessary to the Regional Government high officials, other appointees, public electees, employees, and private sector participants in order to ensure the observation of rule of law;

h) Conducts the compilation, summary, and codification of the laws of the Region and the Federal Government applicable in the Region, and maintains and disseminates the laws of the Region as a representative;

i) In order to develop the awarenes of society for law, provides awareness of law education to the Region society through various methods;

፰ የጠበቆች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የሰነዶች ምዝገባን በተመለከተ፤

ሀ/ በክልሉ ፍርድ ቤቶች ለሚከራከሩ ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ስራቸውን ይቆጣጠራል፤ የጠበቆችን ዲሲፕሊን ጉዳዮች አይቶ ይወስናል፤ በሕግ መሰረት ይሰርዛል፤

ለ/ ለጠበቃ የመክፈል አቅም ለሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ነጻ የጥብቅና አገልግሎት የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፤

ሐ/ በክልሉ ለሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሕጋዊነት በማረጋገጥ ይመዘግባል፤ ይደግፋል፤ ያስተባብራል፤ ሥራቸውን በሕግ አግባብ እና በተመዘገቡበት ዓላማ መሰረት ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ በሕግ መሰረት ይሰርዛል፤

መ/ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ዓመታዊ የሥራና የገንዘብ እንቅስቃሴ ሪፖርት በዚህ ሕግ በተወሰነው መሠረት ይመረምራል፤

ሰ/ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ የውስጥ አስተዳደር እና የራስ አስተዳደር ሥርዓት

8) Regarding Registration of Advocates, Civil Society Organizations and Documentations;

a) Issues licenses to advocates and law firms who litigate in the region courts, renews them, supervises their work, examines and decides on the disciplinary matters of advocates, revokes according to the law;

b) Facilitates access to free legal services for members of the community who cannot afford to pay for an advocate;

c) Registers, supports, coordinates and ensures the legality of civil society organizations functioning in the Region; makes necessary follow-up and supervision to ensure that they carry out their work in accordance with the law and objective for which they are registered, revokes them according to the law;

d) examines the annual work and financial activity report of civil society organizations in accordance with this law;

e) Provides necessary support for civil society organizations to have an administrative system that ensures

እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤

ረ/ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት በሀገሪቱና በክልሉ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ፣ ሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ እና የልማት እንቅስቃሴ ያላቸውን ሚና አስመልክቶ ተገቢውን ጥናት ያካሂዳል፤ የክልሉን መንግሥት ያማክራል፤

ሰ/ በክልሉ ብቻ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን ቁጥር፣ የተሰማሩባቸውን ቦታዎች፣ የሥራ ዘርፎች፣ የተጠቃሚዎቻቸውን እና የአባሎቻቸውን ብዛት እና መሰል መረጃዎች የሚይዝ የመረጃ ማዕከል ያቋቁማል፤ እንዲሁም እነዚህን መረጃዎች ይተነትናል፤ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ያሰራጫል፤

ሸ/ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ንብረት ማስተላለፍና ማስወገድን በተመለከተ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ እርምጃ ይወስዳል፤

ቀ/ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሲፈርሱ በሒሳብ አጣሪነት የሚያገለግሉ ባለሙያዎችን ዝርዝር ከክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፤ ሥራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ይቆጣጠራል፤

በ/ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሰነዶችን

transparency and accountability; follows its implementation;

f) Conducts an appropriate study regarding the role of the civil society organization in the building of the democratic system, protection of human rights and development activities in the Region; advises the Regional State;

g) Establishes an information center that contains the number of organizations registered and working only in the region, their areas where they are engaged, areas of work, the number of their clients and members, and similar information, and analyzes this information and disseminates it through various means of communication;

h) Followups and supervision regarding transfer and disposal of property of civil society organizations; takes measure;

i) prepares a list of experts who will serve as auditors when civil society organizations are dissolved; supervises the proper performance of their work;

j) verifies, registers, revokes, repeals

ያረጋግጣል፤ ይመዘግባል፤ ይሽራል፤ ይሰርዛል፤

፱ ሰብዓዊ መብቶችን በተመለከተ፡-

ሀ/ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን በተመለከተ የሚቀርቡ አቤቱታዎችንና ቅሬታዎችን ይመረምራል፤ እንዲመረመሩ ያደርጋል፤

ለ/ የክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች እቅድ የሰብዓዊ መብት ጉዳዮችን ያካተተ ስለመሆኑ በቅርብ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

ሐ/ ነፃ የሕግ ድጋፍ አሰጣጥ ስትራቴጂዎችን ይቀርፃል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤ በመስኩ የሚሰማሩ አካላትን ያስተባብራል፤

መ/ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በፌደራል ደረጃ የወጣው የብሔራዊ ሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሀ-ግብር በክልሉ ውስጥ ያለውን ተፈፃሚነት ይከታተላል፤ በክልል-አቀፍ ደረጃ ተሳታፊ የሚሆኑትን አካላት እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያቀርባል፤

ሠ/ በፖሊስ ጣቢያና በማረሚያ ቤት ጥበቃና ቁጥጥር ሥር ያሉ ሰዎችን ይጎበኛል፤ አያያዛቸውና ቆይታቸው በሕግ መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል፤ ሕግን ተላልፈዋል በተባሉ ሰዎች ላይ በሕግ መሠረት እርምጃዎችን ይወስዳል ወይም እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

documents according to the relevant law;

9) Regarding Human Rights:

a) investigates complaints and grievances about human rights violations, and causes them to be investigated;

b) Closely follows and supports whether the plans of the Regional Government Offices include human rights matters;

c) sets free legal aid delivery strategies, follows their implementation, coordinates entities engage in the field;

d) Follows the implementation of the National Human Rights Action Plan issued at the Federal level in cooperation with the concerned bodies; coordinates the activities of participating bodies at the Regional level; provides reports to relevant bodies;

e) visits persons under the protection and supervision of police stations and prisons; Ensures that their handling and stay is performed in accordance with the law; take or cause to be taken legal action against persons alleged to have violated the law;

ረ/ የክልሉ ሕብረተሰብ ሰብዓዊ መብቶቹንና ግዴታዎቹን በውል ተገንዝቦ ሕግ አክባሪና አስከባሪ እንዲሆን በተለያዩ ዘዴዎች የሰብዓዊ መብትና የንቃተ-ሕግ ትምህርት ይሰጣል፤ በዘርፉ የተሰማሩ አካላትን እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፤

ሰ/ሀገሪቱ ያፀደቀቻቸው ወይም የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በክልሉ ውስጥ ያላቸውን ተፈጻሚነት ይከታተላል፤

ሸ/ እንደ ሥርዓተ-ጾታና ኤች አይ ቪ ኤድስ ያሉ ዘርፈ-ብዙና ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ያካተቱ የሰብዓዊ መብት ተግባራትን ያከናውናል፤

ቀ/ ሰብዓዊ መብትን የሚመለከቱ ፕሮጀክቶችን ያስተባብራል፤ ይደግፋል፤ ይከታተላል፤

በ/ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት በኩል ጥያቄ ሲቀርብለት ሀገሪቱ የተቀበለቻቸውን የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ብሔራዊ የአፈፃፀም ሪፖርት በማዘጋጀት ረገድ ይተባበራል፤ ያግዛል፤

፲) የዓቃቤ ሕግ የውሳኔ አሰጣጥ እና የፍቅደ ሥልጣን አጠቃቀም ወጥነትን ለማረጋገጥ በፍትህ ሚኒስቴር የፀደቀ መመሪያ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

f) To make the community of the region awared of human rights and obligations in terms of the law and to be respecting the law and cause the law to be respected; provides human rights and law-awareness education through various methods, and coordinates the activities of the bodies engaged in the field;

g) Follows the implementation of the international and continental human rights conventions that the country has approved or accepted in the region;

h) carries out human rights activities that include diverse and vulnerable parts of society such as gender and HIV/AIDS;

i) coordinates, supports and follows projects related to human rights;

j) When the request is provided from the concerning bodies, cooperates and supports in preparing the national implementation report of the human rights conventions accepted by the country;

10) Ensures the implementation of directive ratified by the Ministry of Justice to ensure consistency in decision-making and the use of licensing authority by the public prosecutor;

፲፩) በዓቃቤያን ሕግ የሚሰጡ ውሳኔዎች በሕግ መሰረት መከናወናቸውን የሚያረጋግጥ የሕግ ኦዲትና የኢንስፔክሽን ክፍል ያደራጃል፤ ጉድለቶችን በጥናት አስደግፎ ይለያል፤ በግኝቱ መሠረትም እንዲታረሙ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሲሆን እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤ መልካም ተሞክሮዎችን ይቀምራል፤ ያስፋፋል፤

፲፪) ከግብር ጋር የተያያዙ የይግባኝ ሥራዎችን ያስተባብራል፤

፲፫) በክልሉ የሚከናወኑ የወሳኝ ኩነቶች ተግባራትን በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፣ አፈጻጸሙንም ይገመግማል፤

፲፬) የዐቃቢያነ ሕግ ደመወዝና ጥቅማጥቅም የየወቅቱን ኢኮኖሚና የገበያ ሁኔታ እያጠና በየአምስት ዓመቱ ማሳተካከያ እያደረገ በዋና ጉባዔ ያጸድቃል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል። ዝርዝሩ በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣው በዐቃቢያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፤

፲፭) የክልሉን ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤ ይከታተላል፤ ያስተባብራል፤ የሕግ ታራሚዎች ይቅርታ የሚያገኙበትን ስርዓት

11) Organizes a legal audit and inspection unit to ensure that the decisions made by the public prosecutor are carried out in accordance with the law; identifies the violations based on research and based on the findings, make to be corrected; when necessary, takes action or effects action to be taken, uses and enlarges role models;

12) Coordinates tax-related appeals;

13) Leads principally vital events activities in the Region; supervises; monitors and evaluates its performance;

14) Approves salaries of public prosecutors and benefits will be approved by the Main Council after studying the current economic and market situation; implemdnts up on its approval, details shall be determined by the administrative regulaion of the public prosecutor to be issued by the Administrative Council;

15) Principally manages, supervises and coordinates the activities of the Region Prisons Administration Commission, sets a system for legal prisoners to be

ይዘረጋል፤ ታረሚዎችን የማረምና ማነፅ ሥራዎችን፣ በዘርፉ የሚደረጉ ጥናቶችንና የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ያስተባብራል፤

pardoned, coordinates corrections and rehabilitation of prisoners, coordinates studies and training in the field;

፲፮) የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ በማስደገፍ ብዘሀ-ማዕከላትን ያማከለ የተቀላጠፈ ወረቀት አልባ የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲተገበርና እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

16) By supporting the institution's service delivery with information communication technology, facilitates the implementation and expansion of efficient, paperless service delivery centered on multi-centres;

፲፯) ሌሎች ሕግ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ወይም ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

17) Performs other powers and functions given by law or functions that help to execute its objectives;

**አንቀጽ ፯. ሹመት**

፩) የፍትህ ቢሮ ኃላፊ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልል ምክር ቤት ይሾማል፤

፪) ምክትል ቢሮ ኃላፊው በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሾማል፤

፫) በዞን ደረጃ ያሉ የፍትህ መምሪያ ኃላፊዎች በየአስተደደር እርከኑ ዋና አስተዳዳሪ አቅራቢነት በየእርከኑ ባሉ ምክር ቤቶች ይሾማሉ፤

፬) በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር ያሉ የፍትህ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በየአስተደደር

**Article 7 Appointment**

1) Head of Justice Bureau shall be appointed by the Region Council up on the approval of the Chief Executive;

2) Deputy Heads of Justice Bureau shall be appointed by the Chief Executive of the Region;

3) Heads of the Department of Justice at the Zonal levels shall be appointed by the councils at each level up on the recommendation of the chief administrator of each administrative level;

4) Heads of Justice office in wereda and city administration shall be appointed by councils at each level upon the

እርከኑ ዋና አስተዳዳሪ ወይም ከንቲባ ወይም ስራ አስፈፃሚ አቅራቢነት በየእርከኑ ባሉ ምክር ቤቶች ይሾማሉ፤

፭) በየትኛውም ደረጃ የሚሾም ኃላፊ በሕግ ትምህርት እውቅና ካለው ተቋም የተመረቀ መሆን አለበት፡፡

**አንቀጽ ፰. የፍትህ ቢሮ አወቃቀር**

ፍትህ ቢሮ:-

፩) የፍትህ ቢሮ ኃላፊና እና ምክትል የፍትህ ቢሮ ኃላፊዎች፤

፪) የሥራ ዘርፎች፤

፫) የማኔጅመንት ኮሚቴ፤

፬) የክልል ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ዋና እና ንዑስ ጉባዔ ፤

፭) በዓቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቀጠሩ ወይም የተመደቡ ዓቃቢያነ ሕግ፤ እና አስፈላጊ ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

**አንጽ ፱. የፍትህ ቢሮ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር**

፩) የቢሮው ኃላፊ የፍትህ ቢሮ የበላይ ኃላፊና የካቢኔ አባል በመሆን በሙያውና በሕግ መሠረት ቢሮውን

recommendation of the chief administrator or mayor of each level of administration;

5) An appointee appointed at any level shall be a law graduate from a recognized institution.

**Article 8. Structure of the Justice Bureau**

Justice Bureau:

1) Head of Justice Bureau and Deputy Heads of the Bureau;
2) Work divisions,
3) Management Committee,
4) Regional public Prosecution Main Council and Sub Council;
5) Public Prosecutors employed or assigned according to the regulations of the Public prosecutor; and necessary employees.

**Article 9. Powers and Functions of the Head of Justice Bureau**

1) Head of the Bureau is head of the Justice Bureau and a member of the cabinet, and leads and manages the Bureau by his profession and according to the law;

ይመራል፤ ያስተዳድራል፤

፪) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የቢሮው ኃላፊ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) በምክትል ቢሮ ኃላፊ እንዲሁም በየእርከኑ ባሉ የፍትህ መምሪያ ወይም ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች የዓቃቤ ሕግ ስራ አስመልክቶ የተሰጡ ውሳኔዎችን ያፀድቃል፤ ያሻሽላል፤ ይለውጣል፤ ይሽራል፤ ወይም ጉዳዩ እንዲጣራ ወይም እንደገና እንዲታይ ያደርጋል፤

ሐ) ዓቃቢያነ ሕግን በዓቃቢያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እንዲሁም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህጎች መሰረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ በሕግ መሰረት ያሰናብታል፤

መ) የፍትህ ቢሮን ስትራቴጂክ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

ሠ) ለፍትህ ቢሮ በተፈቀደለት በጀት እና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ

2) Without prejudice to the provision of sub-article1, Head of the Bureau shall have the following powers and functions:-

a) Implement the powers and Functions of the Bureau referred to under Article 6 of this proclamation;

b) Approves, amends, changes, annuls the decisions made by the heads of the deputy head of the bureau and by the heads of the public prosecutor department or office at each level, or causes the case to be investigated or reconsidered;

c) Employees, administers, and dismisses public prosecutors according to the regulations of the public prosecutors and supportive staff according to the civil service laws of the Region;

d) prepares the strategic plan and budget of the Bureau, and implements upon its approval;

e) expends money according to the approved budget and work

ወጪ ያደርጋል፤

ረ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደርጉ ግንኙነቶች ቢሮውን ይወክላል፤

ሰ) የቢሮውን የሥራ አፈጻጸም እና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለመንግስት ያቀርባል፤

ሸ) ለሥራ ቅልጥፍናና ውጤታማነት በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለምክትል ቢሮ ኃላፊ፣ ዓቃቤያነ ሕግና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤

ቀ) በሕግ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**አንቀጽ ፲. የምክትል ቢሮ ኃላፊዎች ሥልጣንና ተግባር**

ምክትል ቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነታቸው ለቢሮው ኃላፊ ሆኖ፣

፩) ለቢሮ ኃላፊ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር የቢሮ ኃላፊውን ያግዛሉ፤

፪) የሚመደቡባቸውን ዘርፎች ይመራሉ፤ ያስተዳድራሉ፤

፫) በቢሮው ኃላፊ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናሉ፤

program for the Bureau;

f) Represents the Bureau in dealings with third parties;

g) prepares and submits performance and accounting report of the Bureau to the government;

h) To the extent necessary for work efficiency and effectiveness, may delegate his powers and Functions to deputy heads of the bureau, public prosecutors and employees;

i) Performs other Functions granted by law.

**Article 10 Powers and Functions of Deputy Heads of the Bureau**

Deputy Heads of the Bureau shall be Accountable to the Head of the Bureau and:-

1) Assist head of the Bureau in planning, organizing, directing and coordinating the powers and Functions assigned to the head of the Bureau;

2) Leads and administers the division to which they assigned for;

3) Performs tasks assigned by the head of the Bureau;

፬) የቢሮው ኃላፊ በማይኖርበት ጊዜ ውክልና ያልተሰጠ እንደሆነ በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ቢሮ ኃላፊ የቢሮ ኃላፊ ሥራን ተክቶ ይሰራል።

**አንቀጽ ፲፩. ከሹመት ስለመነሳት**

የቢሮው ኃላፊ እና ምክትል ቢሮ ኃላፊዎች እንዲሁም በየእርከኑ የሚገኙ የፍትህ መምሪያ ወይም ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች በሾሟቸው አካል ውሳኔ በሹመት ከያዙት ኃላፊነት ሊነሱ ይችላሉ።

**አንቀጽ ፲፪. የዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር**

የዓቃቤያነ ሕግ አስተደደር በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ የዓቃቢያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል።

**አንቀጽ ፲፫. የዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባዔ እና ንዑስ ጉባዔዎች**

፩) በቢሮው የዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባዔ፣ በቢሮውና በዞን ፍትህ መምሪያ የዐቃቢያነ ሕግ አስተዳደር ንዑስ ጉባዔ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪) የዋና ጉባዔው ሰብሳቢ የቢሮው ኃላፊ ይሆናል፤ የጉባዔውን አባላት፣ የአሠራር ሥነ-ሥርዓትና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች የመስተዳድር ምክር

4) In the absence of the head of the Bureau, if no delegation has been granted to the deputy head of the bureau, who has the priority in appointment, shall act in place of the head of the bureau.

**Article 11 Resignation**

The head of the bureau and the deputy head of the bureau, as well as the heads of the Justice department or office at each level, may resign from their positions.

**Article 12. Administration of Public Prosecutors**

The administration of the Public Prosecutor shall be determined by the Regulations of the Public Prosecutor to be issued by the Administrative Council.

**Article 13. Main and Sub- Public Prosecutor Administration Council**

1) The Main Council of the Bureau of public Prosecutors and the Sub Council of public Prosecutors of the Bureau and Zonal Justice Department have been established by this Proclamation;

2) The chairperson of the Main Council shall be head of the bureau; the members of the assembly, the procedure and other details are determined by the regulations of the

ቤት በሚያወጣው የዓቃቢያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፤

፫) ዋና ጉባዔው የራሱ ጽህፈት ቤት፣ ለስራው የሚያስፈልጉ ዓቃቢያነ ሕግ እና በቢሮው ኃላፊ የሚሰየም የጽህፈት ቤት ኃላፊ ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ሙያዊ ነፃነትና ተጠያቂነት

### አንቀጽ ፲፬. የዓቃቤያነ ሕግ የሙያ ነፃነት

፩) ዓቃቤ ሕግ ሥልጣኑንና ተግባሩን ሲያከናውን ከማንኛውም ሰው ወይም አካል ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆኖ በሕግ መሠረት ብቻ ይፈፅማል፤

፪) ዓቃቤ ሕግ በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ ሕግ ያለባቸው ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሕግ መሰረት የተሰጣቸውን ስልጣንና ተግባር በማከናወናቸው ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት የሕግ ተጠያቂነት የለበትም፤

፫) ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ቢሮው ሃላፊ እውቅና ሊያዝ ወይም ሊታሰር አይችልም፡፡

### አንቀጽ ፲፭. ተጠያቂነት

በየትኛውም ደረጃ ያለ ዓቃቤ ሕግ በሥራ

public prosecutor to be issued by the administrative council;

3) Main Council shall have its own office, public prosecutors needed for the work and head of office appointed by head of the Bureau.

## PART THREE

## Professional Independence and Liability

### Article 14. Professional Independence of Public Prosecutors

1) Public prosecutor shall discharge its powers and Functions based on law independently free from any person or body’s interference;

2) Without prejudice to liability under this Proclamation or other laws, public prosecutors shall not be legally liable for any damage caused by the exercise of their powers and Functions under this law or any other law;

3) Any prosecutor who commits a crime punishable by rigorous imprisonment cannot be arrested or detained without the approval of the head of the bureau unless in the case of flagrante delicto.

### Article 15. Accountability

Disciplinary liability of a public prosecutor at

አፈፃፀሙና በሥነ-ምግባር ለሚያሳየው ጉድለት የዲስፕሊን ተጠያቂነቱ በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣው የዓቃቢያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ይሆናል፡፡

any level for his work performance and unethical conduct shall be liabile according to the Administrative Regulations of the Public Prosecutor's to be issued by the Administrative Council.

**አንቀጽ ፲፮. አቤቱታ የማቅረብ መብት**

፩) ዓቃቤ ሕግ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው በየደረጃው ለሚገኙ ኃላፊዎች አቤቱታ የማቅረብ መብት ይኖረዋል፤ አቤቱታ የቀረበለት ኃላፊ ጉዳዩን በአፋጣኝ አጣርቶ ውሳኔ መስጠት አለበት፤

፪) አቤቱታ የቀረበለት ኃላፊ ጉዳዩን ለማጣራት አግባብ ያላቸውን ባለሙያዎች የሚያካትት ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፤

፫) አቤቱታውን የመረመረው ኃላፊ የሕግና የማስረጃ ምክንያቱን በመጥቀስ በበታች ዓቃቤ ሕግ የተሰጠውን ውሳኔ ለማጽደቅ፣ ለማሻሻል፣ ለመለወጥ፣ ለመሻር፣ ለማገድ ወይም ጉዳዩን አስቀድሞ አይቶ ወደ ወሰነው ክፍል ለመመለስ ይችላል፤

፬) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ ፫ መሰረት በተሰጠው ዉሳኔ ቅሬታ ያለዉ አካል ቅሬታውን ደረጃውን ጠብቆ እስከ ክልል ፍትህ ቢሮ ድረስ በየእርከኑ ላሉት የበላይ ኃላፊዎች ማቅረብ ይችላል፤ ሆኖም የፍትህ ቢሮ ኃላፊ ውሳኔ የመጨረሻ

**Article 16. Right to Lodge Appeal**

1) Any person who has grievance against the decision of public prosecutor has the right to lodge complaint to the heads at different levels; a head received complaint shall urgently inquire and give decision;

2) A head received complaint may form a committee containing relevant professionals to investigate the case;

3) A Head considering the complaint may suspend, change, modify, revoke or approve the decision of the subordinate public prosecutor or return the case to the party that saw the case previously by stating his legal and factual reasons;

4) A party who has a complaint against the decision given in accordance with sub-article 3 of this article may submit the complaint to the higher officials at each level up to the Region Justice Bureau; provided, however, the decision of the

ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፲፯. ጥቆማ ወይም አስተያየት የማቅረብ መብት**

፩) ማንኛውም ሰው በፍትህ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር ውስጥ የሚወድቅ ማንኛውም መታረምና መስተካከል አለበት የሚለውን ጉዳይ ወይም ተፈጽሟል የሚለውን የሥነ-ምግባርና የሕግ ጥሰት በማናቸውም መንገድ ለፍትህ ቢሮ እንዲሁም በየአስተዳደር እርከኑ ላሉት ኃላፊዎች ጥቆማ ወይም አስተያየት ለማቅረብ ይችላል፡፡

፪) በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት ጥቆማዎችና አስተያየቶች የሚቀበሉ አካላት የቀረቡላቸውን ጥቆማዎችና አስተያየቶች የሚቀበሉባቸው፣ የሚያጣሩባቸው፣ የእርምት እርምጃዎችን የሚወሰዱባቸውና ይህንኑ ለሕብረተሰቡ የሚገለጹባቸው የአሠራር ሥርዓቶች ይዘረጋሉ፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ ፲፰. የመተባበር እና የመፈጸም ግዴታ**

፩ በክልል ፍትህ ቢሮና በየደረጃው ባለ የፍትህ መምሪያ ወይም ጽህፈት ቤት የሚሰሩ ዓቃቤያነ ሕግ በሕግ የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባራት በሚያከናውኑበት ጊዜ ትብብር የተጠየቀ ማንኛውም ሰው ከአቅም በላይ

Head of Justice Bureau shall be final.

**Article 17. The Right to Whistleblow or Complaint Submission**

1) Any person may submit whistleblow or complaint on any matters that falls within the jurisdiction and function of the Justice Bureau to the Justice Bureau and the officials at each level of administration in any way regarding the matter that shall be corrected and rectified or the violation of ethics and law that has been committed;

2) In accordance with sub-article 1 of this article, the parties receiving complaint and comments shall establish procedures for receiving, checking, taking corrective measures, and reporting the same to the society.

## PART FOUR

## Miscellaneous Provisions

**Article 18. Duty to Cooperate and Perform**

1. When the public prosecutors working in the regional justice bureau and in the justice department or office at every level perform their powers and Functions given by law, any person who is requested to cooperate is

ያልሆነ እና በራሱ ላይ ጉዳት የማያስከትልበት እስከሆነ ድረስ የመተባበር ግዴታ አለበት፤

፪) ማንኛውም የፖሊስ አባል የዓቃቤ ሕግን የመጨረሻ እና ሕጋዊ ውሳኔ የማክበር እና የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ ፲፱. የወንጀል ተጠያቂነት**

፩) ፍትህ ቢሮ እና ዓቃቤያነ ሕግ ሥራቸውን በነፃነት እንዳያከናውኑ ጣልቃ የሚገባ ወይም የሚሰጡትን ህጋዊ ውሳኔ የማያከብርና የማያስፈጽም እንዲሁም የመተባበር ግዴታውን የማይወጣ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ይጠየቃል፤

፪) ማንኛውም የፖሊስ አባል የዓቃቤ ሕግን የመጨረሻ እና ሕጋዊ ውሳኔ በመቃወም ያልታዘዘ እንደሆነ አግባብ ባለው ሕግ በወንጀል ይጠየቃል፡፡

**አንቀጽ ፳ በጀት**

የክልል ፍትህ ቢሮ ከመንግስት በሚመደብለት በጀት ይተዳደራል፡፡

**አንቀጽ ፳፩ የሂሳብ መዛግብት**

፩)ቢሮው የተሟላና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪)የቢሮው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ

obliged to cooperate as long as it is not force majeure and does not cause harm to himself;

2. Any member of the police is obliged to respect and execute the final and legal decision of the public prosecutor.

**Article 19. Criminal liability**

1) Anyone who interferes with the bureau of justice and prosecutors to carry out their work freely, or who does not respect and execute the legal decisions they give, and who does not fulfill the duty of cooperation, shall be prosecuted by the appropriate criminal law;

2) Any member of the police who oppose the final and legal decision of the public Prosecutor and reject order shall be liable with a crime under the relevant law.

**Article 20. Budget**

The Region Justice Bureau shall be administered by the budget allocated from the government.

**Article 21. Books of Accounts**

1) The Bureau maintains complete and accurate accounting books;

2) The books of account and financial

ሰነዶች በክልል ዋና ኦዲተር ወይም በዋና ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

documents of the Bureau shall be examined annually by the Region Auditor General or an auditor appointed by the Auditor General.

**አንቀጽ ፳፪. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

፩) የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፤

፪) ፍትህ ቢሮ ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፤

፫) ቢሮው በሕግ መሰረት ለህዝብ ይፋ እንዳይደረጉ ከተከለከሉ ሚስጥራዊ ሰነዶች በስተቀር በየጊዜው የሚያወጣቸውን መመሪያዎች በማናቸውም መንገድ እንዲታተሙ እና እንዲሰራጩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**Article 22. Power to Issue Regulation and Directive**

1) The Regional Executive Council may issue regulations necessary to implement this proclamtion;

2) The Bureau of Justice may issue directives necessary to implement this proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article;

3) The Bureau may publish and distribute the directives to be issued from time to time by any means, except for confidential documents that are prohibited from being disclosed to the public by law.

**አንቀጽ ፳፫. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

**Article 23. Unapplicable Laws**

Any law inconsistent with this Proclamation shall not apply to the matters covered under this Proclamation.

**አንቀጽ ፳፭. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በክልል ምክር ቤት ከፀደቀበት ታህሳስ 05 ቀን 2ሺ16 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**Article 25. Effective Date**

This proclamation shall enter into force on the date of December 15, 2023, when it was approved by the Region Council.

| | |
|---|---|
| **አርባ ምንጭ**<br>**ታህሳስ 05 ቀን 2ሺ16 ዓ.ም**<br>**ጥላሁን ከበደ**<br>**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር** | **Done at Arba Minch**<br>**December 15, 2023**<br>**Tilahun Kebede**<br>**Chief Executive of South Ethiopia Regional State** |